**የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን <u>አዋጅ ቁጥር </u>858/2006 <u>ለማሻሻል</u>የተዘጋጀ የረቂቅ አዋጅ ማብራሪያ**

**<u>መግቢያ</u>**

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በሬድዮ ዘርፍ ላለፉት 87 ዓመታት እንዲሁም በቴሌቪዥን ዘርፍ ላለፉት 57 ዓመታት ከመንግስት እና ከህዝብ የተጣለበትን ሃላፊነት ለመውጣት የተለያዩ አደረጃጀቶን በመጠቀም ህብረተሱቡን የማሳወቅ፣ የማስተማር እና የማዝናናት አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ ኮርፖሬሽኑ ከህዝብ እና ከመንግስት የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዲችል በየወቅቱ ከነበረው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ጋር የራሱን አደረጃጀት በማስተካከል ሲሰራ ቆይቷል፡፡

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በአዋጅ ቁጥር 858/2006 መሰረት ኮርፖሬሽን ሆኖ ከመቋቋሙ በፊት በ1967 የኢትዮጵያ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ድርጅት በሚል በአዋጅ ቁጥር 15/1967 ተቋቁሞ ሲሰራ ቆይቶ ከዘመነ ደርግ ማብቃት በኋላ የተቋሙ አደረጃጀት እንደገና ተፈትሾ ተቋሙ በ1987 በአዋጅ ቁጥር 114/87 እንደ አዲስ የኢትዮጵያ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ድርጅት ሆኖ ሲቋቋም ተጠሪነቱ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲሆን የተደረገ ሲሆን አዋጁ በዋናነት ዓላማው ያደረገው የሚዲያውን ባህሪይ ታሳቢ በማድረግ በተለይ በጋዜጠኛው እና በቴክኖሎጂ ዘርፉ ያለውን የሰው ሃይል ይዞ ለማቆየት እንዲረዳው ለጋዜጠኛው እና ለቴክኖሎጂ ዘርፍ ሰራተኞች ተቋሙ በራሱ የደመወዝ ስኬል ለመወሰን እንዲችል እድል የሰጠው ቢሆንም የተቋሙን ሰራተኞች ለሁለት በመክፈል የአስተዳደር ዘርፉ በሲቪል ሰርቪስ ህግ እንዲተዳደር እንዲሁም ጋዜጠኛው እና የቴክኒክ ሰራተኛው ደግሞ በተቋሙ መዋቅር መሰረት እንዲስተዳደር በማድረጉ በአንድ ተቋም ሁለት አይነት አሰራር እንዲዘረጋ እና ይህም በተለይ በአስተዳደር ዘርፍ ለነበረው ሰራተኛ ከፍተኛ የቅሬታ ምንጭ ሆኖ ቆይቷል፡፡

ከዚህ ውጪ አዋጅ ቁጥር 114/87ም ሆነ ይህንን አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 78/1989 የላይሰንስ ፊ / የቴሌቪዥን ግብር እና እድሳት ክፍያን/ በሚመለከት ምንም ማሻሻያ ሳያደርግ ቀርቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ምንም እንኳን የ1967 አዋጅ እና ደንብ ከወጣ ከ 40 ዓመታት በላይ ቢሆነውም የቴሌቪዥን ፍቃድ እድሳት ክፍያ መጠን በዚያው በ50 ብር ተገድቦ እንዲቆይ የተደረገ ሲሆን የኮርፖሬሽኑ ቦርድ በ2002ዓ.ም ባወጣው መመሪያ የቴሌቪዥን ፍቃድ ዓመታዊ ክፍያውን ወደ ብር 60 አሳድጎት እስከ አሁን ድረስ በዚሁ መሰረት ሲሰራ ቆይቷል፡፡

ተቋሙ ከላይ እንደተገለፀው ሠራተኛውን በሁለት አይን የሚያየውን አሰራር ለማስተካከል እና የኮርፖሬት አደረጃጀት እንዲከተል በማድረግ ተቋሙን ጊዜው በሚጠይቀው ልክ ለማጠናከር ታስቦ በ2006ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 858/2006 ወደ ኮርፖሬሽን እንዲቀየር የተደረገ ሲሆን በዚህ አዋጅ የኮርፖሬሽኑ ተጠሪነት ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲሁን ተደርጓል፡፡ ሌላው የአዋጁ በጎ ጎን የኮርፖሬሽኑ ሁሉም ሰራተኞች በእኩልነት

እንዲታዩ በማስቻል በሰራተኛው ዘነድ ሲነሳ የነበረውን ትልቅ የመልካም አስተዳደር ችግር ለመቅረፍ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የኮርፖሬት አደረጃጀቱ የፈጠረለትን እድል በመጠቀም ገቢውን ለማሳደግ እጅግ ሰፋፊ ሰራዎች ሲሰራ የቆየ ቢሆንም የቴሌቪዥን ግብር / የላይሰንስ ፊ ክፍያን በሚመለከት የአዋጁ አንቀፅ 21 የ1967 አዋጅ እና ደንብ እንዲቀጥል በመደንገግ አልፎታል፡፡

በሌላ በኩል ኮርፖሬሽኑን ያቋቋመው አዋጅ ቁጥር 858/2006 በአንቀፅ 14 የኮርፖሬሽኑን የገቢ ምንጮች ሲዘረዝር በተለይ በንዑስ አንቀፅ 2 ከመንግስት የሚያገኘውን የበጀት ድጋፍ በተመለከተ በደፈናው ከማስቀመጥ በሰተቀር ግልፅነት የሚጎድለው በመሆኑ ኮርፖሬሽኑ ከመንግስት ለሚጠይቀው የበጀት ድጋፍ ጥያቄ ተገቢውን መልስ እንዳያገኝ እንቅፋት ሆኖ በመቆየቱ አዋጁን ማሻሻል አሰፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ ከመንግስት ማግኘት የሚገባውን የበጀት ድጋፍ አፈፃፀም በግልፅ ማመላከት አሰፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እንዲሁም የኮርፖሬሽኑ ሰልጣንና ተግባር ከተለያዩ ሁለት አዋጆች መመንጨቱ በአሰራር ላይ ችግር እየፈጠረ በመሆኑ ከላይ የተጠቀሱትን ክፍተቶች ለመፍታት እና የኮርፖሬሽኑን ስልጣን እና ተግባር በአንድ አጣምሮ በያዘ አዋጅ መተካት አሰፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እንዲሁም በአዋጁ የተቀመጠውን የተቋሙን ራዕይ እና ተልእኮ ከሀገራዊ ሪፎርሙ አንፃር እንደገና መቃኘት አሰፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የአዋጅ ማሻሻያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለተከበረው የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

**የአዋጅ ማሻሻያው ዓላማ**

የዚህ አዋጅ ማሻሻያ ዋነኛ አላማ የኮርፖሬሽኑ ራዕይ እና ግብ ከአጠቃላይ ከሀገሪቱ የሪፎርም ለውጥ ጋር አብሮ እንዲሄድ በማድረግ ኮርፖሬሽኑ በሀገሪቱ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ቁልፍ ሚና ለመጫወት እንዲችል ማድረግ ሲሆን ይህ ዓላማ እንዲሳካ በተለይ የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ አቅም የተጠናከረ መሆን ስላለበት የኮርፖሬሽኑን የበጀት ምንጭ በተመለከተ በዚህ የአዋጅ ማሻሻያ ግልፅ ድንጋጌ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

የዚህ የአዋጅ ማሻሻያ ሌላኛው አላማ ከአሁን በፊት ከተለያዩ አዋጆች ይመነጩ የነበሩ የኮርፖሬሽኑ ሰልጣን እና ተግባራት ወደ አንድ ማምጣት ሲሆን ከዚህ አንፃር የቴሌቪዥን የአገልግሎት ክፍያን በማሻሻል እና በዘመናዊ አሰራር በመደገፍ የላይሰንስ ፊ ገቢ የኮርፖሬሽኑ ዋነኛ የፋይናንስ ምንጭ እንዲሆን ማስቻል ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ የቴሌቪዥን የአገልግሎት ክፍያ አተገባበር ሰርዓት ግልፅነት እና ተጠያቂነት ያለበት በማድረግ ግዴታቸውን በማይወጡ ግለሰቦች እና ተቋማት የህግ ተጠያቂነት እንዲኖርባቸው ማስቻል ነው፡፡

**<u>የአዋጅ ማሻሻያው አሰፈላጊነት</u>**

የኢተዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን እንደ የህዝብ ሚዲያ የአራተኛ መንግስትነት ሚናውን በተግባር እንዲወጣ ለማስቻል እና በሀገረ መንግስት ግንባታ ሥራ ንቁ ተሳታፊ መሆን እንዲችል ጠንካራ የህግ ድጋፍ እና የፋይናንስ ምንጭ ሊኖረው ይገባል፡፡

ከዚህ አንፃር የኮርፖሬሽኑን አላማ፣ ስልጣን እና ተግባራት በግልፅ በማስቀመጠ እንዲሁም የኮርፖሬሽኑ ሥራ አመራር ቦርድ ተቋሙን በተሻለ ሁኔታ የሚደግፍበትን ስርዓት በማስቀመጥበእንዲሁም የኮርፖሬሽኑ የበጀት ምንጭ በተለይም ከመንግስት ለኮርፖሬሽኑ ሊሰጠው የሚገባውን የበጀት ድጋፍ በግልፅ በማመላከት በኩል አዋጁን ማሻሻል እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ የኮርፖሬሽኑ ዋነኛ የፋይናንስ ምንጭ መሆን የሚገባው የቴሌቪዥን የአገልግሎት ክፍያ ስርዓት በጠንካራ ህግ እና አሰራር ባለመደገፉ ምክንያት ተቋሙ ማግኘት የሚገባውን ገቢ እንዳያገኝ እና ራሱን የዘመነ ቴክኖሎጂ ባለቤት እንዳይሆን ተደርጎ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ይህ የአዋጅ ማሻሻያ የቴሌቪዥን አገልግሎት ክፍያን በማሻሻል እና በዘመናዊ አሰራር እንዲደገፍ በማድረግ ህብረተሰቡ ግዴታውን በቀላሉ እንዲወጣ የሚያስችል ስርዓት የሚፈጥር ሲሆን በሌላ በኩል ግዴታቸውን የማይወጡ የቴሌቪዥን ባለቤቶች ላይ ጠንካራ የሆነ የህግ ተጠያቂነት ለመፍጠር እንዲቻል ይህ የህግ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>በአዋጅ ማርቀቁ ሂደት የተሳተፉ አካላት እና ለረቂቁ ግብዓት የሆኑ ህጎች</u>**

የአዋጅ ረቂቁን ሲያዘጋጅ እንደ ግብዓት ከተጠቀመባቸው መካከል የ1967 አዋጅ ቁጥር 15/1967 ደንብ ቁጥር20/1967፣ አዋጅ ቁጥር114/1987 እና የተሻሻለ የኢትዮጵያ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ድርጅት አዋጅ ቁጥር78/1989 እንዲሁም አሁን በሰራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን አዋጅ ቁጥር 858/2006እና አዲሱ የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 የሚገኙበት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የሌሎች አለም አቀፍ ሚዲያዎች አሰራር ለአዋጅ ማሻሻያ ረቂቁ እንደ ግብዓት ተወስዷል ፡፡

የአዋጁ የመጀመሪያ ረቂቅ ከተዘጋጀ በኋላ ከኮርፖሬሽኑ ማኔጅመንት ጋር ውይይት የተደረገበት ሲሆን ከማኔጅመንት የተገኙ ግብአቶችን በማካተት ለሠራተኛ ውይይት እንዲቀርብ ተደርጎ ሠራተኛው የሰጠው ግብአት እንዲካተትበት ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም በማኔጅመንት እና በሰራተኛው የተሻሻለው ረቂቅ ለኮርፖሬሽኑ ሥራ አመራር ቦርድ ለውይይት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ቦርዱ በረቂቅ አዋጁ ላይ ሰፊ ውይይት በማድረግ የማዳበሪያ ሃሳብ በመስጠት ረቂቅ አዋጁ ለሙያዊ እይታ ለፍትህ ሚኒስቴር እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም የጠቅላይ አቃቢ ህግ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በረቂቅ አዋጁ ላይ የሰጡት አስተያየት እንዲካተት ተደርጎ የመጨረሻውን ቅርፅ ሊይዝ ችሏል፡፡

**<u>የአዋጁ አደረጃጀት</u>**

የአዋጁን አደረጃጀት ስንመለከት አዋጁን ለማውጣት ያስፈለገበትን ምክንያት ሚያብራራ መግቢያ ያለው ሲሆን በአራት ክፍሎች እና በ28 አንቀፆች የተደራጀ ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል ስለአዋጁ ስያሜ እና ትርጓሜ የሚደነግግ ክፍል ሲሆን በሰሩ ሁለት አንቀፆችን ይዟል። ሁለተኛው ክፍል በአጠቃላይ ስለ ኮርፖሬሽኑ መቋቋም ፣ አላማ ስልጣን እና ተግባር እንዲሁም የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ እና ከፍተኛ አመራሮች አወቃቀር፣ ስልጣን እና ተግባር እንዲሁም የኮርፖሬሽኑን የበጀት ምንጭ በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎችን የያዘ ሆኖ በ14 አንቀፆች  የተደራጀ ነው። የአዋጁ ሶስተኛው ክፍል በዋናነት ትኩረት ያደረገው የቴሌቪዥን ባለቤትነት ምዝገባ እና የላይሰንስ ፊ ክፍያ ጉዳይ ላይ ሲሆን በሰሩም 6 አንቀፆችን ይዟል። የአዋጁ የመጨረሻው እና አራተኛው ክፍል ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን በዋናነትም አዋጁን ለማስፈጸም እንዲረዳ ኮርፖሬሽኑ ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት፣ የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች አስተዳደርን የተመለከቱ ድንጋጌዎች፣ የተሻሩ አዋጆች፣ ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ስልጣንን የተመለከቱ ጉዳዮችን የያዘ ሆኖ በሰሩ 6 አንቀፆችን ይዟል።